# ድምጻችን እንዲሰማ እንፈልጋለን!

በስዊድን የሚገኙ አካል ጉዳተኛ ስደተኞች የህይወት ተመክሮ ታሪክን በፎቶግራፍ መግለፅ -- በዲዜብልድ ሬፊውጂ ዌልካም (DRW) የተዘጋጀ የፎቶ ቮይስ ፕሮጀክት



Independent Living Institute
independentliving.org

DISABLED REFUGEES WELCOME

MED STÖD FRÅN ALLMÄNNA ARVSFONDEN

ገደቦች:

- በጣም ጠባብ
- የመኖሪያ ቦታ ምርጫ አለመኖር
- ለአካል ጉዳተኛ ተደራሽ አለመሆን
- ለአካል ጉዳተኛ በሚመች መልኩ ማስተካከያ አለመደረጉ
- የህክምና ማስረጃ ለአካል ጉዳተኛ ተደራሽ የሆነ ቤት ለማግኘት አለመርዳቱ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነገሮች ከማድረግ ተከላክሎናል:

- ውጭ ከመውጣትȶ
- ስዊድንኛ ቋንቋ ከመማር
- ምግብ ከማብሰል
- ገላ ከመታጠብ
- ልጆቻችንን ከመንከባከብ


እነዚህ ሁሉ ችግሮች በመጨረሻ ከዚህ በታች ወደተዘረዘሩት ሁኔታዎች ይመራሉ:

- ከማህበረሰቡመገለል
- ከማህበረሰቡ መነጠል
- ጥገኛ መሆን
- የስነልቦና ችግሮች
- የጤንነት አደጋ

# የመኖሪያ ቤት

## የግል እንክብካቤ






“ መታጠቢያ ቤቱ እንደ እኔ ፍላጎት አልተስተካከለም ፣ ስለዚህ ባለቤቴ መርዳት ነበረበት፡፡ እንዲሁም የገላ መታጠቢያው በመሰበሩ ምክንያት ውሃው በየቦታው ሁሉ ይረጫል እና ወለሉ እርጥብ እና ተንሸራታች ይሆናል። ይህም የመውደቅ ትልቅ አደጋ ስላለው ብዙ ጊዜ ለሳምንት ያህል ገላዬን አልታጠብም፡፡ እኔ ብቻ ሳልሆን ልጄንም ገላዋን ማጠብ አልቻልኩም

“ ይህ መታጠቢያ ቤቴ ነው ፡፡ እዚያ አንድ ጉብታ አለ። ገላዬን በምታጠብበት ጊዜ እግሮቼን የሚደግፈውን የአካል ድጋፍ ማውለቅ አለብኝ፡ ፡ ያለ እሱ መቆም አልችልም ተንሸራታችም ይሆናል። ሁልጊዜ ገላዬን ስታጠብ የመውደቅ አደጋ ያጋጥመኛል ብዬ እሰጋለሁ፡፡ ስለዚህ ተስፋ አስቆራጭ ነው፡፡

## ምግብ ማብሰል/ ልጆችን መንከባከብ






“ የምኖርበት ቤት የማብሰያ ክፍል ባለመኖሩ የምንተኛበት ክፍል ውስጥ ቆሜ ማብሰል ግዴታዬ ነበር። የሚጠጣ ውሃ እንኳን ከሽንት ቤት ነበር የምቀዳው። ስቆም ስለሚደክመኝ ብዙ ጊዜ ወድቄአለው። ቤቱን ያከራየን ሰውዬ በሳምንት ሁለት ጊዜ ብቻ ነበር ምግብ እንዳበስል የሚፈቅድልኝ፤ እሱንም በትገደበ ሰዓት ነው። ስለዚህ ለልጄ የሚሆነውን ምግብ ብቻ ሰርቼ እኔ የምበላውን ለማብሰል የግድ ወደ ጎረቤት መሄድ ነበረብኝ።

“ አካል ጉዳተኛ ነኝ፤ህጻን ልጅም አለችኝ። ቤቴ ጠባብ በመሆኑ ምክንያት አልጋ ላይ እንቀመጣለን፣ አልጋ ላይ እንበላለን፣ አልጋ ላይ እንተኛለን። ሁሉም እንቅስቃሴ አልጋ ላይ ብቻ ነው። ልጄ መሬት ወርዳ የምትጫወትበት ቦታ እንኳን የለም በዚህም ምክንያት እንደ እኩዮቿ በጊዜ መራመድ አልቻለችም ነበር።

“ የዶክተር ሰርቲፊኬት አግኝቼ (ስለ መኖሪያ ቤት ፍላጎት ሁኔታዬ) ለማዘጋጃ ቤቱ ሰጠሁኝ፣ ግን ከእነሱ ምንም ምላሽ አልሰማሁም፡፡

---



## የምኖሪያ ቤት ቅርጽ


“ ቦታው ለአልጋ ብቻ ነው የሚበቃው፡፡ ይህ አጠቃላይ ክፍሉ ነው። ሁለት ሰዎች እዚህ ይኖራሉ፣ ቀን እና ሌሊት አልጋ ላይ ነን፡፡

“ በመስኮት በኩል ነው የምተኛው፣ እናም ቅዝቃዜ በመጣ ቁጥር ስለሚያመኝ እንቅልፍ ሳይወስደኝ አድራለሁ በዚህም ምክንያት ብዙ ጊዜ ትምህርት ቤት እቀራለሁ፡፡ ይህንን ችግሬን በማየት ሐኪም የህክምና ወረቀት (ለሌላ መኖሪያ ቤት የምስክር ወረቀት) ሰጠኝ፡፡ እስካሁን ግን መልስ የለም፡፡



“ ምንም ነገር ማግኘት ቀላል አይደለም፤ ሆኖም ግን አንድ ቤተሰብ ቤት ውስጥ ፎቅ ላይ አንድ ክፍል ቤት አገኘሁ። ቤቱ ለኔ ምቹ ባለመሆኑ ምክንያት ከደረጃ ላይ መውደቅ ለኔ የተለመደ ነገር ነበር።

“ በእጄ ብርጭቆ እንኳን ይዤ መሄድ አልችልም፤ ምንም ነጻነት የለኝም።



“ እጆቼ ጠንካራ ስላልሆኑ የተከራየሁትን ቤት በር ለመክፈት ለእኔ በጣም ከባድ ነው፤ በዚያ ላይ ደግሞ ልጅ አለኝ፡፡ ከቤቱ አከራዮች ጋር የመጀመሪያ/ ቀጥታ ውል ስለሌለኝ ለአንዳንድ ተከራዮች እንደሰጡት ለእኔ አውቶማቲክ የበር መክፈቻ ሊሰጡኝ አልቻሉም፡፡


የመኖሪያ ቤት....

ሃኪሟ ቁስሎቼን ስትመለከት ከደረጃ በወደኩኝ ቁጥር ራሴን እንደምጎዳና ይህም የሆነው በምኖርበት ቤት አለመመቸት መሆኑን ስነግራት በጣም በመደንገጥ ያለብኝን የጤና ችግር የሚገልፅ የህክምና ማስረጃ ምስክር ወረቀት ጽፋልኝ ነበር። ሆኖም ግን ማንም ሊረዳኝ የቻለ የለም


ለእኔና ለልጄ የመኖሪያ ቤት እየፈለኩ ነበር። ተሃድሶ ባለሞያዋ እና ሐኪሜ ፍላጎቴን የሚያረጋግጡ የምስክር ወረቀቶችን ጽፈዋል ፡፡ ነገር ግን በማዘጋጃ ቤቱ ውስጥ ያለው ኃላፊ ‘ይህ የእኔ ሥራ ነው’ ፤ ‘ዶክተሩ የራሱ የሆነ ሥራ አለው’ ነበር ያለኝ።

# ደረጃ፤ ደረጃ፤ በጣም ብዙ ደረጃዎች


ወደ ስዊድን ከመጣሁ ጊዜ ጀምሮ የአካል ጉዳተኝነቴ ተሰምቶኝ አያውቅም ምክንያቱም እዚህ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሁኔታ አለ። ለምሳሌ የትራንስፖርት አገልግሎት ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ምቹ ሆኖ ነው የተሰራው። በአብዛኛው ቦታ ከደረጃ መወጣጫ ጎን አሳንሰር አለ። ኢትዮጵያ እያለሁ ከቤት ወጥቼ አንድ ቦታ ደርሼ እስክመለስ ድረስ በሰው ላይ ጥገኛ መሆን የግድ ነው ምክንያቱም ለአካል ጉዳተኛ ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ፡፡




ብዙ ጊዜ እዚህ ቦታ ያለው አሳንሰር ይበላሻል፤ ችግሩ ደግሞ አንድ መውጫ ብቻ ነው ያለው ስለዚህ ያለኝ አማራጭ አንድ ፊርማታ በባቡር ሄጄ መውጣት ነው።



ይሄ ፎቶ የሚያሳየው የምኖርበት ቦታ ያለውን ደረጃ ነው፤ ከአሳንሰር እንደወረድኩኝ እነዚህን ደረጃዎች ነው የማገኘው። በወጣሁ በገባሁ ቁጥር እነዚህን ደረጃዎች መውጣት እና መውረድ ይጠበቅብኛል። በዚህም ምክንያት በየቀኑ የሚላኩልኝን ፖስታዎች ማየት አልችልም። ቶሎቶሎ ልብሶቼን እንዳላጥብም ሆኛለሁ፤ እቃ ገዝቼ ስገባ በጣም ነው የምቸገረው ምክንያቱም ተሸክሜ ደረጃ መውጣት ስለማልችል።




አሳንሰር ሲበላሽ



የመኖሪያ አፓርትመንት እፈልግ ነበር እናም አንድ ክፍል 3ኛ ፎቅ ላይ አገኘሁ ሆኖም ግን ህንጻው አሳንሰር ስለሌለው ቤቱን ልከራየው አልቻልኩም።




አንዳንድ ጊዜ እዚያ ሲደርሱ ተንቀሳቃሽ ደረጃው አይሰራም። በስብሰባዎች ላይ ዘግይቼ ስገባ ሰዎች ‹የአፍሪካ ሰዓት› ይላሉ ፤ ግን አንዳንድ ጊዜ ምክንያቱ የተንቀሳቃሽ ደረጃ መበላሸት ነው፡፡



ይህ ስዕል አፓርታማዬን ከውጭ ያሳያል፡፡ ወደ ዋናው በር ለመምጣት እነዚህን ደረጃዎች መውጣት አለብኝ፣ ሌላ መንገድ የለም፡፡ ወደዚያ በሄድኩ ቁጥር ፍርሃት ይሰማኛል፤ በክረምት ወቅት ያለውን ሁኔታ ባልናገረው ይሻላል፡፡

ወደዚህ እየመጣሁ እያለ የባቡር ጣቢያው አሳንሰር ተበላሽቶ አገኘሁት፤ በዚህ ጣቢያ ተንቀሳቃሽ ደረጃ ባለመኖሩ ባቡር ለመያዝ ረጅም ደረጃዎችን ቀስ እያልኩ መውጣት ነበረብኝ በዚህም ምክንያት ልይዘው ያሰብኩት ባቡር አመለጠኝ።



2ኛ ፎቅ ላይ እኖራለሁ፣ በቀላሉ በማንኛውም ሰዓት መውጣት የምችልበት ቦታ አይደለም፡፡ ግን ወደ ውጭ የምወጣው ለአንድ ምክንያት ብቻ ሳይሆን ብዙ ምክንያቶች እስካሉ ድረስ ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት ለብዙ ዓመታት ስዊድሽ ቋንቋ ለመማር መሄድ አልቻልኩም፡ ፡ ደረጃውን ስወጣ እና ስወርድ የሚረዳኝ ሰው እፈልጋለሁ፡፡

እንደ አለመታደል ሆኖ አሳንሰሮችና ተንቀሳቃሽ ደረጃዎች ሁሌም አይሰሩም እና ደግሞ ሁሉም ቦታ አይኖሩም።

# አለመግባባት? መድሎ?

ለምንድነው ግን ሰዎች በተለይም ምእራባዊያን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ሲያገናኙን እርዳታ ሲያስፈልገን እኛን ለመርዳት ዝግጁ የሚሆኑት፣ የሚያዳምጡን? በተለያዩ መንገዶች ግን ወደ መስሪያ ቤታቸው ስንሄድ ከዚያ ሙሉ በሙሉ የተለዩ ናቸው፣ ይህ ያስገርመኛል። እነዚህ ሰዎች በቢሮ ውስጥ ሲሆኑ ለምን አይሰሙም? ወደ ቢሮ ስንሄድ አያዳምጡንም፡፡ ለምን እንደሆነ አልገባኝም፡፡

ለምን

- የተሻለ ስለማያውቁ ነውን?
- እነሱ ስላልፈለጉ ነው?
- በሕጎቻቸው ምክንያት ነው?
- የአካል ጉዳተኛ ስለሆንን ነው?
- ጥቁር ስለሆንን ነው?



## በመጠለያ ውስጥ

በመጠለያ ውስጥ ከተደራራቢው አልጋ የላይኛውን ሰጡኝ፡፡ትንጠላጥየ መውጣት እንደማልችል ስነግራቸውም አልሰሙኝም፡፡ የሕክምና የምስክር ወረቀት ጠየቁኝ፡፡

የላይኛውን አልጋ አገኘሁ። የመጠለያው ሠራተኞች ወደ ተለያዩ ክፍሎች ወሰዱኝ፣ ነገር ግን በሁሉም ክፍሎች ውስጥ የላይኛው አልጋዎች ብቻ ነበሩ ያልተያዙት፡ ፡ ሆኖም ግን በታችኛው አልጋ ላይ ተኝተው ከነበሩ ሰዎች ጋር መነጋገር ጀመርኩ፣ እናም ከእኔ ጋር ለመቀያየር ፈቃደኞች ነበሩ፡፡



## በመጓጓዣ አገልግሎት ውስጥ

ከፊት ወንበር ላይ ሲቀመጡ የበርዎን መዝጊያ በቀኝ እጅዎ መዝጋት አለብዎት፡፡ እኔ ደግሞ በቀኝ እጄ ላይ በደረሰብኝ ህመም ይሄንን ማድረግ አልችልም። የአካል ጉዳቴ ስለማያስታውቅ በአብዛኛው የታክሲ አሽከርካሪዎች አይረዱኝም፡ ፡ እርዳታ ትፈልጋለች ብለውም አይገምቱም፡፡ በግራ እጄ ለመዝጋት ስሞክር ሚዛኔን አጣሁ እና ወደ ታች ልወድቅ ነበር፡፡ ይህ ለእኔ የዕለት ተዕለት ተሞክሮ ነው፡ ፡ አሽከርካሪዎች ሊረዱኝ የሚሞክሩት ሁሌም አንድ ነገር ሲከሰትብኝ ብቻ ነው።

## በተንቀሳቃሽ ደረጃ ላይ


ባለብኝ የአካል ጉዳት ተንቀሳቃሽ ደረጃዎችን መጠቀም እችላለሁ ነገር ግን ጉዳቴ በቀኝ የአካል ክፍሌ በመሆኑ ሁሌም የምይዘው የተንቀሳቃሽ ደረጃውን የግራ መደገፊያ/ እጀታ ነው ይህ ቦታ ደግሞ በተለምዶ ሰዎች ሲቸኩሉ ለመቅደም የሚጠቀሙበት ነው እና እኔ እዛ ቦታ ላይ ቆምኩ ማለት ማለፍ የሚፈልጉ ሰዎችን መንገድ ዘጋሁ ማለት ነው። በዚህም ምክንያት አንዳንድ ሰዎች ገፍትረውኝ ይሄዳሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በጣም ይናደዱብኛል ይህ የሆነው ደግሞ የኔ አካል ጉዳት ካልተናገርኩ በስተቀር ለሰው በግልጽ የሚታይ ባለመሆኑ ነው። ሁሌም ባይሆን አንዳንዴ በቀኝ በኩል የማልቆመው ሚዛኔን መጠበቅ ስለማልችል እንደሆነ ስናገር አንዳዶቹ ሲረዱኝ ሌሎቹ ግን ይሄ የኛ ጉዳይ አይደለም በዚህ ምን አስኬደሽ አሳንሰር አትጠቀሚም ነበር ይሉኛል። ሲናደዱብኝ ይሁን ግድየለም ይናደዱ ብዬ ዝም የምልበት ቀንም አለ።

## በካፌ ውስጥ

አንድ ቀን ሁሌ የምገባበት ካፌ ውስጥ በመጥፎ ሁኔታ ተስተናገድኩ። ካፌው የአንድ ባልና ሚስት ሲሆን ባልየው በጣም በጥሩ ሁኔታ ነው የሚያስተናግደኝ። ሚስትየው ግን ገንዘቤን ከፍዬ እንደምስተናገድ እያወቀች እንኳን በስነ-ስርዓት እንደሌሎች ደንበኞቿ አታስተናግደኝም። መጠጫ ብርጭቆ እንኳ ስጠይቅ የምትሰጠኝ ቆሻሻ እና ለሌሎች ደንበኞች የማትሰጠውን ነው።

## በመጠጥ ቤት ውስጥ

ወደ መጠጥ ቤቱ ውስጥ እንዳልገባ ከለከሉኝ። ጥቁር ስትሆን በቃ እንደዚህ ነው።



# በጨለማ ውስጥ ያለ ብርሀን



ብዙ ችግሮች ነበሩኝ፣ ብቻዬን ነበርኩ፡፡ ከወዳጆቼ በጣም ርቄ ነበር፡፡ ማንንም አላውቅም. እዚህ ካሉ ሰዎች ጋር ጊዜ ማሳለፍ ከባድ ነው፡፡ ብቸኝነት ሲሰማኝ በጫካው ዙሪያ እራመዳለሁ ፡፡ በራስ የመተማመን ስሜታችንን አጥተናል።

በኪ ውስጥ በረዶ አለ፣ ስለሆነም በአካል ድጋፍ ዎከር መንቀሳቀስ አስቸጋሪ ነው። ያ ጊዜ በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ፈተና ነበር፡፡ ሁሌም በረዶ ውስጥ እግሬ ይቀረቀርና መውጣት ያቅተኝ ነበር እናም አንድ ሰው እስኪረዳኝ ድረስ መጠበቅ ነበረብኝ።

የአካባቢውን አውቶቡስ ለማግኘት ለ45 ደቂቃዎች በእግር መሄድ ይኖርብዎታል፡ ፡ አንዴ ለቃለ መጠይቅ (የጥገኝነት ሂደትን በተመለከተ) በተጠራሁ ጊዜ ኢሚግሬሽን ካምፕ መኪና ስላላቸው እንዲያደርሱኝ ጠየኩኝ፡፡ እነሱ ግን ወደ ሌላ ቦታ መሄድ አለብን ብለው ጥለውኝ ሄዱ፡፡ ያንን ርቀት (ወደ አውቶቡስ ማቆሚያው) መሄድ እንደማልችልም ብነግራቸው በጭራሽ አልሰሙም፡፡ መኪና በማጣት ብቻ ሦስት ጊዜ ቃለ-መጠይቅ አመለጠኝ፡ ፡ አቤቱታ ለማቅረብ ወዴት መሄድ እንዳለብኝም አላውቅም፡፡

የጥገኝነት ሂደት በጣም ያልተረጋጋ ነበር ፡፡ እኔ በብዙ የተለያዩ ቦታዎች ውስጥ ተቀምጬ ነበር፣ አንዳንዴ ለአንድ ወር፣ አንዳንዴ ለሁለት ሳምንት። የተለያዩ ቦታዎች አንዳንድ ጊዜ እንደ ካምፕ፣ አንዳንድ ጊዜ ሆቴል፣ የአደጋ ጊዜ ማረፊያ ውስጥ ሁሉ ተቀምጬ ነበር፡፡ ለሦስት ዓመታት በሆቴል ውስጥ አስቀመጡኝ፡፡ ከአልኮል እና ከአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኞች ጋር አንድ ላይ ነበር ያስቀመጡኝ። ከዛ ግን ወደ ሰሜን ሌላ ከተማ እንደሚልኩኝ ነገሩኝ፡ ፡ እኔም በዚህ ከተማ አንድ የስራ ልምምድ internship እያደረኩ እንደሆነና አሁን ካለሁበት ማዘጋጃ ቤት ቅርብ ቦታ ቢያስቀምጡኝ ልምምዱን እንምከታተልና ስጨርስም ስራ አግኝቼ ራሴን እንደምችል ብነግራቸውም ሊሰሙኝ ግን አልቻሉም፡፡

አፓርታማዬን በአንድ ወር ውስጥ ለቅቄ መውጣት አለብኝ፣ የምሄድበት ቦታ የለኝም፣ መልስም አላገኘሁም፡፡ ችግሮቹ መቼም አያቆሙም። እቅድ ማውጣትም ሆነ ስለ ወደፊቱ ማሰብ ከባድ ነው፣ ምን እንደሚፈጠር አላውቅም፡፡ በአካል ጉዳቴ የተነሳ አፓርታማዎችን መፈለግ ከባድ ነው፡፡ ምን እንደማድረግም አላውቅም የሕክምና የምስክር ወረቀቶች አይረዱም፣ ማንም አያዳምጠኝም፡፡ ወደ ትምህርት ቤት መሄድ እፈልጋለሁ እና ተምሬ ሥራ መስራት እፈልጋለሁ ግን አልችልም፡፡ ነገ ምን እሰራለሁ፣ ማንን አገኛለሁ ብዬ ከማሰብ ይልቅ ሁሌም የማስበው ነገ ምን ይፈጠራል፣ የት ይወስዱኛል፣ ይሄ ስጋት መቼ ነው የሚያበቃው የሚለው ሀሳብ ነው የሚያስጨንቀኝ።

ሁሉ ነገር ለእኔ ጨለማ ነው፡፡ ማሰብ አልችልም፣ ማቀድ አልችልም፡፡ የማስታወስ ችግር አለብኝ ፣ አንጎሌ አይሠራም፡፡

ይገርማል ችግሮቻችን በጣም ተመሳሳይ ናቸው። በተለያዩ ቦታዎች ውስጥ ብንገኝም ሁላችንም እንሰቃያለን፡፡ እንደዚያ የሆነው ለምንድን ነው? ችግሮቻችንን ግን ለምን አይፈቱልንም?።

ወፏን እና የፀሐይ ብርሃኑን ብልጭታ ስመለከት ብሩህ ጊዜያት መኖራቸውን ያስታውሰኛል ወፏ ደግሞ የሰላምና የተስፋ ተምሳሌት ናት፡፡

ተስፋ አልቆርጥም፣ ተስፋ ማድረጉ ጥሩ ነው፡፡ ተስፋ ሳልቆርጥ እታገላለሁ፡፡ መሄድ ወዳለብኝ ሁሉም ቦታዎች ሁሉ እየሄድኩ ችግሬን መግለጽ አላቋርጥም፡፡ ለብዙ ሰዎች እናገራለሁ ምናልባት የተወሰኑት ያዳምጡኝ ይሆናል፡፡

# ማህበራዊ ሕይወት



“ሰዎች አንድ ላይ ተሰብስበው ሳይ ፎቶ ማንሳት እፈልጋለሁ፤ እኔ ግን ብቻዬን ቁጭ ብያለሁ።

“አገራችን ብቸኛመሆን አይቻልም፣ እዛ የብቸኝነት ችግር የለም፣ እዚህ ስሆን ብቻ ነው ብቸኝነት የማይሰማኝ።

“ይሄ ፎቶ ስቶክሆልም ውስጥ ጥሩ ጊዜ ሳሳልፍ ነው የሚያሳየው። እዚህ መጠጥ ቤት ውስጥ የሚመጡትን ሰዎች በአብዛኛው አውቃቸዋለሁ እና ደግሞ ቤቱ ውስጥ መጠጥ እርካሽ ነው ሰዎቹም በጣም ተጫዋቾች ናቸው።

“ይህ ፎቶ ዘና ያደርገኛል እና በራስ መተማመኔን ያሳያል፣ የነፃነት ስሜት ይሰጠኛል፡፡









“ይህ በተለምዶ ሴት ልጅ በእርግዝና እና ከወለደች በኋላ ዘመድ ወይ ጓደኛ በቡድን ተሰብስቦ የሚበላው የኢትዮጵያ ባህላዊ ምግብ ነው።

“የጋራ ልምዶችን ለሌላው ማካፈል በራስ መተማመን እና ጥንካሬን ይሰጣል፡፡



## ስለ አውደ ርዕዩ

እ.ኤ.አ በ2019 የበጋ ወራት በስዊድን የሚገኝ አንድ የአካል ጉዳተኛ ስደተኞች ቡድን የአካል ጉዳተኝነት ህይወት በስዊድን ምን እንደሚመስል ለመወያየት በተለያዩ ቀናት ተሰባስበው ነበር። በእያንዳንዱ ስብስባቸው ወቅት አንድ ርዕሰ ጉዳይ በመምረጥ ይህንኑ ርዕስ በፎቶግራፍ በማስደገፍ አጉልተው ለመቅረብ ተስማሙ። ሲገናኙ የውይይት አጀንዳቸው የሚሆነው ያነሷቸው ፎቶግራፎች ነበሩ። በሰበሰቧቸው ፎቶግራፎች አውደ ርዕይ ለማሳየት ተስማሙ እና አንድ ላይ በመሆን አውደ ርዕዩ ላይ የሚነቀርቡ ርዕሶችን፣ ፎቶግራፎችን፣ እሱን የሚገልፁ ፅሁፎችን እና በምን አይነት ቅርፅ ይቅረብ የሚለውን ውሳኔ በመወሰን ተለያዩ።

ይህ አውደ ርዕይ በስቶክሆልሙ ኢንዲፔንደንት ሊቪንግ ኢንስቲትዩት (Independent Living Institute) ስር ባለው በDRW ፕሮጀክት የሚመራ  የፎቶቮይስ ፕሮጀክት ውጤት ነው። ይህ ፕሮጀክት በሳይንሳዊ ጽሑፍነትም ለህትመት ይበቃል፡፡

## ፎቶቮይስ

ፎቶቮይስ አሳታፊ የምርምር ዘዴ ሲሆን ተሳታፊዎች በራሳቸው ሕይወት ውስጥ ባለሞያዎች የሆኑበት ነው፡፡ በዚህ ዘዴ የዕለት ተዕለት ሕይወታቸውን ለመመዝገብ እና ለማየት ታሪኮችን ለመናገር ፎቶግራፎችን ይጠቀማሉ፡፡ ተሳታፊዎቹ አስፈላጊ ናቸው በሚሉት ጉዳዮች ላይ የተመረጡ ፎቶዎች እና ታሪኮች በቡድኑ አባላት ተቀነባብሮ ለኤግዚቢሽን፣ ለመጽሐፍ ወይም ለድረ-ገፅ አገልግሎት ሊውሉ ይችላሉ፡፡

### ተሳታፊዎች

ሔለን
ሊሊ
አስቴር
ክፍሌ
ማህሌት
ጁሊየስ
ሳራ
ኤሊያስ

### የፕሮጀክቱ አመቻቾች

ራሄል አበባው (የDRW ሠራተኛ እና የአማርኛ ተርጓሚ)
ጄሚ ቦሊንግ (የILI ዳይሬክተር እና የDRW ፕሮጀክት መሪ)
ዶሮቲ ሪድል (የተሃድሶ ባለሞያ ቴራፒስት)